## Amharic
## 2020 Transportation Letter and Safety Procedures During COVID-19

የተከበራችሁ ወላጆች/አሳዳጊዎች

ልጅዎ ትራንስፖርት ለመገልገል የሚችል ወይም የማይችል መሆኑን የሚጠቁም መልዕክት እስካሁን ሊደርስዎት ይገባል። የልጅዎን ትራንስፖርት በተመለከተ መረጃ ካልደረስዎት እባክዎ ከትራንስፖርት ክፍሉ ጋር በ 617.349.6862 ወይም tfisher@cpsd.us ይነጋሩ።

ልጅዎ ትራንስፖርት መገልገል የሚችል ሆኖ ነገር ግን በዚህ አመት የትምህርት ቤት አውቶቡሱን **የማይጠቀም**ከሆነ፣ እባክዎ ከትራንስፖርት ክፍሉ ጋር በ 617.349.6862 ወይም tfisher@cpsd.us ይነጋገሩ።

አብዛኛው ቤተሰብ በመጀመሪያው የትምህርት ቀን ልጆቻቸው አውቶቡስ ከሚጠቀሙ ይልቅ ልጆቻቸውን እራሳቸው ወደ ትምህርት ቤት መውሰድ የሚመርጡ ሲሆን ይህንንም ማድረግ ይችላሉ። ይሁን እንጂ፣ ልጅዎ ለተከታታይ አምስት ቀናት አውቶቡስ የማይጠቀም ከሆነ፣ ከእርስዎ እስካልሰማን ድረስ የልጅዎ መውረጃ ቦታ ከትራንስፖርት መስመሩ ላይ ሊነሳ ይችላል።

ልጅዎ Cambridge ውስጥ ወደሚገኝ ሌላ አድራሻ በአውቶቢስ ለመሄድና ከዛም ለመምጣት ካስፈለገው (እንደ ልጅ እንክብካቤ ባሉት ስምምነት ምክንያቶች የተነሳ)፣ እባክዎ የልጅዎን ትምህርት ቤት ያግኙና አድራሻውን ይስጧቸው።

የበለጠ የደህንነት መረጃዎችና እንደ የእኛን Bus Tracker እና Bus Stop Finder ያሉ አጋዥ መሳሪያዎችም እንዲሁ በድህረ ገፃችን ላይ ይገኛሉ:www.cpsd.us/departments/transportation።

ይህ ጊዜ ለሁሉም ሰው አስቸጋሪ እንደሆነ የምናውቅ ሲሆን ይህንንም ደብዳቤ በጥንቃቄ የሚመለከቱት ስለሆነ እናመሰግናለን።

መልካም እድል ለስኬታማ የትምህርት አመት፣

Tina Fisher፣ CPS የትራንስፖርት ተቆጣጣሪ

**ጭብሎችን በአውቶቡስ ውስጥ ሁልጊዜ ማድረግ ግዴታ ነው**

ህንን ወደ እንግሊዘኛ፣ ስፓኒሽኛ፣ ሃይሺያን፣ ሲሪዮልና አማርኛ መተርጎምና ማስገባት።

## በኮቪድ-19 ወቅት ያለ የደህንነት አካሄዶች

***በአውቶቡስ ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ በሚጓዙበት ወቅት ደህንነቱ የተጠበቀ ጉዞ እንዲያደርጉ ይህንን የደህንነት መረጃዎች ከልጅዎ ጋር መለስ ብለው ይመልከቷቸው።***

***የአፍና አፍንጫ መሸፈኛዎች ያስፈልጋሉ*** አውቶቡስ ውስጥ፣ ተማሪዎች፣ አሽከርካሪዎችና ተቆጣጣሪዎች የአፍና አፍንጫ ጭምብል ወይም የፊት መሸፈኛዎች ማድረግ አለባቸው። ምናልባት ልጆች ረስተው ቢመጡ በሚል፣ ለአስቸኳይ ጊዜ የሚያስፈልጉ የአፍና አፍንጫ ጭምብል ወይም የፊት መሸፈኛዎች በሁሉም ተሽከርካሪዎች ውስጥ ይገኛሉ። አንድ ተማሪ የአፍና አፍንጫ ጭምብሉን ካወለቀ፣ ሁኔታው ከባድ የሆነ የደህንነት አደጋ ስለሚፈጥር ትምህርት ቤቱ ከወላጆች ጋር በመገናኘት የልጃቸውን፣ የአሽከርካሪዎችና የሌሎች ተማሪዎችን ደህንነት ለማስጠበቅ የሚያስችሉ ስትራቴጂዎችን በሚመለከት ይወያያል። አንድ ተማሪ የአፍና አፍንጫ ጭምብል የማያደረግ ከሆነ በአውቶቢስ የመሄድ እድሉን ሊያጣ ይችላል።

***ወደ አውቶቢስ ውስጥ በሚሳፈሩበት ወቅት የሚኖር ደህንነት:*** አውቶቢሱ በማቆሚያው ስፍራ ሲደርስ፣ ተማሪዎች በቻሉት ፍጥነት ቶሎ ብለው ወደ ኋለኛው የአውቶቢሱ ክፍል ይግቡና ባዩት የመጨረሻው ወንበር ላይ ይቀመጡ። በወንበሮቹ ላይ ምልክቶች የሚኖሩ ሲሆን ያም ልጆቹ ተዘበራርቀው እንዲቀመጡ የሚያስታውሳቸው ሲሆን በአንድ ወንበር ላይም አንድ ተማሪ ብቻ ነውም የሚቀመጠው።

***አድራሻዎ በየጊዜው የታደሰ መሆኑን እርግጠኛ ይሁኑ።*** በሚያስፈልገን ጊዜ እርስዎን ለማግኘት እንድንችል፣ እባክዎ ለትምህርት ቤቱ በአሁን ጊዜ ያለዎትን አድራሻና የአስቸኳይ ጊዜ መረጃዎትን መስጠትዎን እርግጠኛ ይሁኑ።

***የአውቶቢስ ማቆሚያ ሰዐቶች የተጠጋጉ ናቸው:*** የ Cambridge የትራፊክ ሁኔታዎችን ከግምት ውስጥ በማስገባት፣ አውቶቡሱ በማንኛውም ቀን በ 10 ደቂቃ ሊዘገይ ወይም ሊቀድም ይችላል። እባክዎ ልጅዎ በአውቶቢስ ስፍራው ከተያዘለት ጊዜ 10 ደቂቃዎች ቀደም ብሎ መገኘቱን ያረጋግጡ።

***ምንም አይነት መጮህ፣ መዝፈንና ቦታ መቀያየር አይቻልም።*** ተማሪዎች ፀጥና ረጋ ብለው መቆየታቸው በጣም አስፈላጊ ነው። የአሽከርካሪውን ትኩረት ከመውሰድ በተጨማሪ፣ ድምፅን ከፍ አድርጎ ማውራት፣ መጮህና መዝፈን የመተንፈሻ በሽታ አስተላለፊ የሆኑ ፍንጣቂዎችን በስፋት የሚሰራጩበት መንገድ መሆኑ ይታወቃል።

***በአውቶቢስ ውስጥ የማይፈቀዱ:*** ስልጣን የሌላቸው አዋቂ ሰዎች፣ እንስሳቶች፣ ሙዚቃ መጫወት፣ እቃዎችን መወርወር፣ መጮህ፣ የመቀመጫ ወንበርን መቀየር፣ የአፍና አፍንጫ መሸፈኛን ማውለቅ፣ የአሽከርካሪዎን ትኩረት መውሰድ፣ የአሽከርካሪውን እይታ መጋረድ

***የመቀመጫ ቀበቶዎችን ማድረግ ይገባል:*** ልክ በራሳቸው የቤት ተሽከርካሪዎች ውስጥ እንደሚያደርጉት ሁሉ፣ ተማሪዎች የመቀመጫ ቀበቶአቸውን መታጠቅ አለባቸው። ለደህንነት ሲባል፣ ተቆጣጣሪው ሰው በአብዛኛው ጊዜያቶች የመቀመጫ ቀበቶን በመታጠቅ ረገድ ሊያግዛቸው ስለማይችል ይህንን ማድረግ አስቸጋሪ ከሆነባቸው እባክዎ በቤት ውስጥ እንዲለማመዱ ያድርጉ።

### ተጨማሪ አካሄዶች ለ 2 ክፍል እና ከዛ በታች ላሉ ተማሪዎች

***አንድ ሰው 2 ክፍልና ከዛ በታች ያሉ ተማሪዎችን በአውቶቡስ ማቆሚያው ቦታ ላይ ሊጠብቃቸው ይገባል።*** ልጁ ማንኛውንም አዋቂ ሰውና በእድሜ ከፍ ያለ ወንድም መለየት ካልቻለ፣ በ Cambridge Rindge and Latin School (459 Broadway, Cambridge) በሚገኝው የSafety and Security ቢሮ እስኪወሰድ ድረስ በአውቶቡሱ ውስጥ የሚቆይ ይሆናል። አንድ ሰው እርስዎን የሚያገኝዎት ሲሆን እርስዎም በ 617.349.6772 ቁጥር Safety/Security ቢሮ መደወል ይችላሉ።

***በአውቶቡስ ውስጥ ቢጫ የአውቶቢስ ማንጠልጠያ መደረግ አለበት።*** በመጀመሪያው የትምህርት ቀን አስተማሪዎች ለተማሪዎች ቢጫ የአውቶቢስ ማንጠልጠያ የሚሰጧቸው ሲሆን ስልክ ቁጥራቸውንና

የት ቦታ ላይ ከሰዐት ከአውቶቡስ እንደሚወርዱ
ይዘረዝራል።

**ጭብሎችን በአውቶቡስ ውስጥ ሁልጊዜ ማድረግ ግዴታ ነው**